# ጎንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴ

ተስፋዬ ሽብሩ እና
ዲ.ያሬድ ገ/መድኅን

እኔና ተስፋዬ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ከባሕር ዳር ተነሥተን በመንገደኞች ማጓጓዣ አውቶቡስ በአስቸጋሪው መንገድ ወደ ጎንደር ጉዞ ጀመርን:: ወረታን አልፈን ተራራማና ጠመዝማዛውን ሥፍራ አቋርጠን ጣራ ገዳም አካባቢ ያለውን ደን ሰናደንቅ ገደሉ ደግሞ ያስፈራል:: መኪኖች ከላይ እየሄዱ ታች ሲታይ በመኪና መሄዳችንን ያጠራጥራል:: አውቶቡሳን ላይ ያለን እስኪመስለን ድረስ ከሥር የምና ያቸው ሜካዎች ሰዓይን ፋቅ ናቸው:: አጠገባችን የነበሩ አንድ ተሳፋሪ እዚህ ከገደሉ ሥር ታች ሜካ ውስጥ ገዳም አለ:: መድኃኔዓለም ገዳም ይባላል:: ብዙ መነኮሳት ይኖራሉ አሉን:: የአባቶቻችን የቦታ ምርጫ የሚገርም ነው::

8:00 ላይ አውቶብሳችን ጎንደር መግቢያ ካለችው ትንሽ ከተማ አዘዞ ደረሰ:: ኮረኮንቹን ጨርሰን አስፋልቱን ያዝን:: መቼም የኮሮኮንቹ መንገድ ሁኔታ ዳግመኛ አያድርስ ያሰብላል:: ያም ሆኖ አለቀና አዘዞ ደረስን:: አዘዞ አባ ሳሙኤል፣ ክብት እርባታ፣ ሳሙና ፋብሪካ፣ ቸቸላ እያልን ወደ ጎንደር ከተማ ተጠጋን:: ከተማዋ ተራራ ላይ ስለሆነች አውቶብሳችን የመጨረሻውን ዳገት ተያይዞታል:: ወደ መሐል ከተማ ለመውጣት እየቃተተ ነው:: ተስፋዬ አጠገቤ በአካል አብሮኝ ቢሆንም በሐሳብ ሄዷል:: የአፄ ፋሲል ሀገር ጎንደርን እያየ ስለ እርሷ ከሰማው ጋር እያገናዘበ ይመስላል::

እንደሚታወቀው ጎንደር ታላላቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት ነግሠውባታል:: የሊቃውንት ምንጭ ናት:: ይህች ከተማ የመላ ኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነበረች:: የነገሥታቱ መኖሪያ፣ የመሳፍንቱ መሰብሰቢያ፣ ለመላ ሀገሪቱ የሚዳረስ አዋጅ የሚታወጅባት ትልቅ ከተማ ነበረች:: ዋና ከተማ የሆነችው ግራኝ መሐመድ ከተሸነፈ በኋላ በአፄ ሠርፀ ድንግል /1563–1597/ ዘመነ መንግሥት ነው:: ቆይቶም አፄ ፋሲል ሲነግሥ /1632–1667/ ጎንደር ማዕከላዊ መንግሥትነቷ ጸንቷል:: ከዚያም የፋሲል ቤተ መንግሥት /ፋሲል ግንብ/ የእድያም ሰገድ ኢያሱ ቤተ መንግሥት ተሠርቶባታል:: 44ቱ ታቦታትም በከተማዋ ተተክለውባታል::

ወደ ጎንደር ከተማ ዘልቀን ከገባን በኋላ ከአፄ ፋሲል ግንብ ፊት ለፊት ስንደርስ ከአውቶብሳችን ወረድን:: ሻንጣችንን ይዘን ወደ ማረፊያችን አመራን::

ወደ ማታ ወተተን የተለያዩ አድባራትን ማየት ጀመርን:: ጎንደር ከተማ የቆየነው ለአምስት ቀናት ነው:: በእነዚህ ቀናት ታላላቁን አድባራት ተዘዋውረን አይተናል:: የቤተ ክርስቲያን አባቶችንም አነጋግረናል::

የሚገርመው በጎንደር ከተማ ከመኖሪያ ቤቱ ታቦታቱ የሚበዙ መሆ ሰላቸው ነው:: በተወሰነ እርምጃ ቤተ ክርስቲያን አለ:: ትንሽ ስትሄዱ በኋላ እልፍ ስትሉ አደባባይ ኢየሱስ እልፍ ስትሉ አባ ጣሚ ሚካኤል፣ መድኃኔዓለም የማታዩት ቤተ ክርስቲያን የለም:: የጎንደር ሕዝብ በታቦታት ተከቧል:: የንጉሡ የፋሲል ቤተ መንግሥት እንኳን በአራቱም ማዕዘን በተተከሉ አብያተ ክርስቲያናት ታቅፏል::

አስቀድሞ ልናያቸው ለቅድ የያዝናቸውን ቦታዎች ለማየት ተነሣን:: ለዚህ ደግሞ ቦታውን የሚያውቅ ሰው ያስፈልገን ነበር:: ዲ.መላኩ በዚህ መሐል ነበር የመጣው:: እናም ቦታዎችን ሁሉ እያዞረ ሊያሳየን ኃላፊነቱን ወሰደ:: በየቦታው ካሉ አባቶች ጋር ይተዋወቃል:: ስለዚህ የእንግዳነት ሲጋታችን በእሱ በኩል ተቃለለ:: በማግሥቱ ዲ.መላኩን ይዘን ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ደብረ ብርሃን ሥላሴ አመራን:: የደብረ ብርሃን ሥላሴ ጥንታዊ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተራራ ላይ ግርማ ሞገስ ለብሶ ሲታይ ልብን ያረካል:: ያየው ሁሉ ጥንታዊ መሆኑን እንዲረዳለት ሆኖ ተቀምጧል::

ዙሪያ ግንቡቹ የፋሲል ግንብ በተሠራበት የአሠራር ዓይነት የታነፁና ጥንታዊ ናቸው:: ያልተጠረቡ ድንጋዮች መሬት ውስጥ ተቀብሮ በቆየ ከኖራ በተሠራ ሲሚንቶ ተያይዘው ቆመው ሲታዩ ለቤተ ክርስቲያኑ ውበት ሰጥተውታል:: የቤተ ክርስቲያኑ ቅጽ ርና ወጥ በሆነ እንጨት የተሠራ ትልቅ ነው:: በሩ ላይ ተሳልመን ስንገባ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ፊት ለፊት አየን:: ሕንፃው በአራት መዓዘን ቅርጽ የተሠራ ሲሆን የተሠራበት ግንብ ጥንታዊ ነው:: ከዚህ ቀጥሉ ያለውን ተስፋዬ ይተርክላችኋል::

## ደብረ ብርሃን ሥላሴና አፄ ኢያሱ

ስለ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ስናነሣ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድን ማውሳታችን የግድ ይሆናል:: የደብረ ብርሃን ሥላሴን ታሪክ አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ነጥሉ ማየቱ ታሪኩን ያደበዝዘዋል:: አፄ ፋሲል ጻድቁ ዮሐንስን፣ ጻድቁ ዮሐንስ ደግሞ ዛሬ ታሪኩን በመጠኑ የምናየውን አድያም ሰገድ ኢያሱን ይወልዳል:: እንግዲህ አፄ ኢያሱ የደጋጎቹ ነገሥታት ልጅ መሆኑ ነው::

አፄ ዮሐንስ ልጃቸውን ኢያሱን በትሕርምትና በሥርዓት በገዳም እንዲያድግ በመፈለጋቸው አፄ ሠርጸ ድንግል ባቀኑት በአርማጭሆ ወደሚገኘው ታላቁ ገዳም ደብረ ሞረና ላኩት:: በዚያም በገዳሙ ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ዜማ ዳዊት አጠናቅቀው ካወቁ በኋላ የገዳሙ ኃላፊዎች ይህንን ልጅ አስተምረነዋል ብለው ወደ አባታቸው ሰደዷቸው:: አፄ ዮሐንስም «ሌላስ ምን ተምሯል?» ብለው ይጠይቃሉ:: ሌላማ ምን እናስተምረው? ይሏቸዋል የገዳሙ አለቆች:: «እንጀራ መጋገር ፣ የአባቶች እግርና ልብስ ማጠብ፣ ሌላም በገዳሙ ያሉ

www.ethiopianorthodox.org

...ማር




አስተምራችሁታል?» ብለው በድጋሚ ቢጠይቁ «ይሄንንማ የጌታችንን ልጅ እንዴት እናዝዛለን ሌላ አርድእት መቼ ታጣና» ይሏቸዋል:: ጻድቁ ንጉሥም «እንግዲያማ ትዕቢት ነው አስተምራችሁ የመጣችሁልኝ በሉ መልሳችሁ ውሰዱት እናንተ መነኮሳት የምትሠሩትን ሥራ በገዳሙ ያለውን ሥርዓት ሁሉ አስተምራችሁ ሳኩልኝ» ብለው መልሰው ሰደዷቸው::

ከዚያም ኢያሱ በገዳም ያለውን ሥርዓት አጠናቅቆ ተምሮ መጣ:: አባቱም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ኃላፊነት ይሰጡታል:: «በገዳሙ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ፣ ንፍሮ በሚበላባቸው ቀኖች ንፍሮ፣ እንጀራ በሚበላባቸው ቀኖች እንጀራ እንዲሆን አድርገህ እንደ ገዳም ሥርዓት ይህንን ቤተ መንግሥት አስተዳድርልኝ» ብለው አባቱ ጻድቁ ዮሐንስ ወራሴ መንግሥት ኢያሱን ያዙዙታል::

ኢያሱ እንደታዘዘው ቤተ መንግሥቱን በገዳም ሥርዓት ማስተዳደር ይጀምራል:: በ1674 ዓ.ም ኢያሱ የንግሥና መንበሩን ከአባቱ ይረከባል:: አሁን ኢያሱ ንጉሥ ሆኗል::

አፄ ኢያሱ በነገሡ በአሥራ ሁለተኛ ዓመቱ በ1686 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ የሚገኘውን የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንን አስተከለ:: በዚሁ ዓመት መቃረቢያ ተሠርቶ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ:: በበዓሉም ላይ አዲስ ተሹሞ የመጣው ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ማርቆስና ለሁለተኛ ጊዜ የተሾመው /እጨጌነቱን/ እጨጌ ጸጋ ክርስቶስ ተገኝተዋል:: በዓሉ በተከበረበት ዕለት አፄ ኢያሱ በትልቅ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሻምላ መዝዞ ታቦቱን አጅቧል:: ወደ መቃረቢያው ሲደርስ ከፈረሱ ወርዶ ታቦቱን አክብሮ ከመቃረቢያው አገባው:: /እዚህ ላይ አፄ ኢያሱ ሥልጣን ክህነት ይኑረው አይኑረው የተገኘ ማስረጃ ስለሌለ እንዲህ ነው ማለት አልተቻለም:: ክህነት ነበረው የሚሉ ግን



ታላላቅ ሊቃውንት ቅኔ አበርክተዋል:: ዓቃቤ ሰዓት ጥበበ ክርስቶስ መመድስና ክልክሎት መናኒ ዓለም የነበረው አባ ቀውስጠስ ሰምና ወርቅ ተቀኝተዋል:: ከነዚህ ቅኔዎች እንዳቸውም በዘመን ታሪክ ውስጥ ተመዝግበው አልተገኙም::

አፄ ኢያሱ ታቦቱን አክብሮ ስለ ማምጣቱ በዘመኑ የተገጠመ የተባለ የአማርኛ ግጥም ይህንን ይመስላል:—

ወዲት ሄዶ ሞጃል ሰሞንኛው ቄሱ
ታቦት ተሸክሞ ዘውድ ትቶ ኢያሱ
የተሸሸገውን ያቡቱን ቅብና
ገለጠው ኢያሱ ታቦት አንግሦ::
እያነው ኢያሱን ደብረ ብርሃን ቆሞ
ተኪናቢል ጋር ሦስቱን ተሸክሞ
ሰውነቱን ትቶ መልአክ ሆኖ ደሞ::
ሥላሴን ቢሸክም ኢያሱ ግንኝ
አራቱ ኪናቢል አምስተኛ ሆነ::

በዚህ ደብር መጀመሪያ የተሾመው ቀውስጠስ ነበረ:: የደብሩም የመጀመሪያ የማሕረግ ስም ሊቀ ካህናት ነበር:: ወዲያው ተለውጦ መልአከ ብርሃን ሆኗል:: ቀውስጠስ ያረፈው በ1716 ዓ.ም በ85 ዓመት ዕድሜው ነበር:: እስከዚያው ድረስ በሹመቱ ቆይቶ እንደሆን የተጻፈ መረጃ አልተገኘም:: የተቀበረው ግን እዚያው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ መሆኑ ይታወቃል::

ታቦተ ሕጉም በመቃረቢያ ውስጥ ለሁለት ዓመት ቆይቶ የዋናው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ጀመረ:: በ1688 ዓ.ም የሕንፃው ሥራ ሲጠናቀቅ ወደ አዲሱ ሕንፃ ገብቷል:: ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራበት እንጨት በጣም ትላልቅ ነበር:: በዚያን ጊዜ በምን መጓጓዣ ሆነው እንደመጡት ሳስተዋል ያስገርማል:: እንጨቱ የመጣው ግማሹ ከዘጌ ነው ሲል የተቀረው ደግሞ ከአርማጭሆ እንደሆነ ይነገራል::

የቀድሞ ሕንፃው ክብ ሲሆን ሦስት መቅደስ ነበረው:: የበሩ /ሳንቃዎች/ ሲከፈቱ አይታዩም፣ ተሽከርክረው ወደ ውስጥ ወደ ግድግዳው ነበር የሚገቡት::

## ስያሜ

አፄ ኢያሱ ቤተ ክርስቲያኑን ካሠሩ በኋላ ታቦተ ጽዮንን ወደ ጎንደር ለማምጣት ወደ አክሱም ጉዞ አድርገው ነበር:: በተለያዩ ምክንያቶች ለማምጣት ሳይቻላቸው ቀርቷል:: በዚህም ቅር ተሰኝተው የአክሱም ጽዮንን አካባቢ ሕዝብ ሦስት ቀን ግብር ከልክለዋቸዋል:: ከዚያም አብረዋቸው የተጓዙት አባ ስብሐት ለአብ የሚባሉ ሰው ሕዝቡ በረሃብ ሊያልቅ ሲል ታቦተ ጽዮንን ማምጣት ባይሳካልን ለምን ታቦተ ሥላሴን አናስገባም አሏቸው:: በዚሁ ተስማምተው ታቦተ ሥላሴ እንዲገባ አድርገዋል:: የአክሱም ታቦተ ጽዮንም ለደብረ ብርሃን ሥላሴ ግብር እንድታስገባ ግብር ጥለውበት ተመልሰዋል::

አፄ ኢያሱ ወደ ሸዋ ደብረ ብርሃን ተጓዘው ሊቃውንቱንና ባለባቱን ጠይቀው ደብረ ብርሃን የሚለውን ስም ለመሰየም ፈቃድ ሲያገኙ ብዙ ወቄት ወርቅ ሰጥተው ተመለሱ:: ይህንን ስያሜ የመረጡበት ምክንያትም ቤታው ብርሃን የወረደበት በመሆኑ በሁኔታው ተማርከው እንደሆነ ይነገራል::

## በጠላት ወረራ ጊዜ

ድርቡሽ የጎንደር ከተማን ሲያቃጥል ሕዝቡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ በመሰባሰብ ጸሎተ ምሕላ ያደርግ ነበር:: ለማዩም በጉምና በጢስ ይሸፈናል:: ቤተ ክርስቲያኑ እንዲጠፋ የፈለጉ ሰዎችም «ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ካልተቃጠለና ካልጠፋ ጎንደር እንዳልጠፋች ይቆጠራል» በማለት ለድርቡሾች መንገድ እየመሩ የመጡበት ጊዜ እንደነበር የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ::

ድርቡሾች በሩን ለመስበር የተቻላቸውን ቢያደርጉም ሳይሆንላቸው ይቀራል:: እንጨት ሰብስበው አቃጥለው ለመግባት ሲሞክሩ በበሩ ላይ የተሣለው የሳንቃው ሚካኤል ሥዕል ሰይፍ እንደመዘዘ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሳይታይ ለእነርሱ ብቻ ይታያቸዋል:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ያለው ከዚህ በታ ነው እንዳትነኩ ብለው ተመልሰው ጥለው እንደሄዱ የሚነገር ታሪክ አለ:: በቤተ ክርስቲያኑ ያሉ አባቶች ይህንን ሥዕል ቄስ ካልሆነ ዲያቆን እንኳን እንዳይነካ በማለት ተከብሮ በዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የሰኔ እና የኅዳር ሚካኤል ዕለት ብቻ እንዲገለጥ ወስነዋል::

አፄ ኢያሱ የዘመነ መንግሥቱ ፍጻሜ በተቃረበበት ወቅት የሥላሴን ቤተ ክርስቲያን በ1685 ዓ.ም በሥዕል ማሠራትና ማስጌጥ ጀምሮ ነበር:: ደብሩ በጊዜው ከከተማ ውጣ ያለ በመሆኑና በእግዚአብሔር ተአምር ከድርቡሽ ወረራ ከመቃጠል ድኗል::

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን የዘመኑ ታሪክ እንደሚያወሳው በ1699 ዓ.ም መብረቅ ቤተ ክርስቲያኑን እንዳቃጠለው ይጠቅሳል:: ይህም በከፊል ይሁን ወይም ሙሉ በሙሉ የተብራራ ነገር የለውም:: የቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንደሚገልጹት መብረቅ አንዱን ጎን ብቻ እንዳልቀረ ያትታሉ:: በአሁኑ ሰዓት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በእርጅና ምክንያት በመድከማቸው ቤተ ክርስቲያኑን ተክተው የሚያስተዳድሩት አባ ጌራ ወርቅ እንዳሉት ደግሞ አፄ ኢያሱ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ ልጁ ዳዊት /ማልሳይ/ እንደገና እንደሠራው ይገልጻሉ:: እኛም ይህንን ለታሪክ ተመራማሪዎች በመተው ወደ ቀረው ታሪክ እናልፋለን:: በውስጡ ያሉት ሥዕሎችም ጊዜ የተሣሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ:: ሥዕሎቹን በወቅቱ የነበረው ጸሐፊ ትእዛዝ ሐዋርያት ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ እንሥሎ ወደ ፊትም እንዲህ ያለ ሥዕል አይኖርም ሲል መስክሯል:: ሥዕሎቹ ትላልቅ ዓይኖች ክብ ፊት ያላቸው የጎንደር ሥዕሎች መታወቂያ ናቸው::

አፄ ኢያሱ ሥዕሉን ያሣሉት ቀለሙን በሽቶ እያስበጠበጡ መሆኑን መምህር ጌራ ወርቅ እንዳሉ ገልጸውልናል:: በሥዕሉ ላይ ያለውን ሽቶ ለመቅሰም ሴቶች ሲሳለሙ ሆን ብለው በልብሳቸው ያሹት ነበር:: ሊቃውንቱም ተው ቢሏቸው አይሰሙም ነበር:: በዚህም እግዚአብሔር ተቆጥቶ በመብረቅ እንደመታው ያስረዳሉ::

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኑን አካባቢ ምሽግ አድርጎት ነበር:: ጠላት በጎንደር ስድስት ዓመት ያህል ሲቆይ በምብ ከአየር ላይ ቢወርድበትም ቤተ ክርስቲያኑ ከቃጠሎ ለመትረፍ ችሏል:: ጣሊያንም ይህ ተአምር ስላስገረመው የቤተ ክርስቲያኑን ክዳን ቀድሞ መምህር ገ/እግዚአብሔር በተባሉ የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ /በኋላ አቡነ መርቆርዮስ ተብለው በሐረር በነበሩ ጳጳስ/ ጠያቂነት በሸክላ አለበሰው:: በኋላ በ1957 ዓ.ም አፄ ኃይለ ሥላሴ ቆርቆሮ አስቀይረው ዙሪያውን አጠናክረው አሠሩለት:: በዚህ ሁኔታ እስከ 1964 ዓ/ም ቆየ:: ባሕል ሚኒስቴርም ጥንታዊነቱን መልቀቅ የለበትም በማለት በቆርቆሮው ላይ እንደቀድሞው ሣር አለበሰው::

በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ የእንቀላል ግንብ በመባል የሚታወቁ ቤቶች አሉ:: በአፄ ኢያሱ ዘመን በ12ቱ ሐዋርያት አምሳያ በዚያው ዘወትር የሚቀመጡ ወደ ከተማ የማይወጡ መቀነን በዚያው እየተሰጣቸው ሰዓቱን እየተከፋፈሉ የሚያጥኑ 12 መነኮሳት ይቀመጡበት ነበር:: በአሁኑ ሰዓት ብዙዎቹ እየፈረሱ ይገኛሉ:: ቀድሞ ባሕል ሚኒስቴር ነበር ለጥገናው የሚንቀሳቀሰው:: አሁን ግን የአካባቢው ነዋሪዎች ለጥገና የሚያስፈልገውን ገንዘብ በማሰባሰብ ከሚቴ አዋቅረው የጥገና ሥራውን እያንቀሳቀሱ ይገኛሉ::

# ደብረ ብርሃን ሥላሴ— ዛሬ

በአሁኑ ሰዓት ከካህናቱና ከምእመናን የዕድሳትና የቅርስ ጥበቃ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ለመጠገን እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: በዚህም መሠረት በከፊል የማሪያውን ሥራ ለመሥራት ተችሏል:: የቀረውን ደግሞ የገንዘብ አቅማቸው ስላልፈቀደላቸው ጊዜ እየጠበቁ ለት ነው::

በደብረ ብርሃን ሥላሴ ቀድሞ ከ170 ካህናት በላይ ያገለግሉ ነበር ተብሎ ይገመታል:: ዛሬ ግን ከ25–30 ቢደርሱ ነው:: ደሞዛቸውም ይህንን ያህል በቂ የሚባል አይደለም:: ቅዳሴ እሑድ በባዓላት፣ በዓብይ ጾም፣ በጾመ ፍልሰታ ይቀዳሳል:: ሰዓታት በዐብይ ጾም እሑድ በጾመ ፍልሰታ የእመቤታችን ክብረ በዓል ዕለት ይደርሳል::

በቤተ ክርስቲያኑ የአብነት ትምህርት /ቅኔ/ ይሰጣል:: ከ150–200 የሚሆኑ ደቀ መዛሙርት ይማራሉ:: ቁጥራቸው ከዚህ የሚጨምርበትም የሚቀንስበትም ጊዜ አለ::

ይህንን ጥንታዊና ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ ይዞቱንና ቅርጹን ሳይለቅ እንደተጠበቀ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ምእመናን አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ ቢችሉ መልካም ይሆናል::

ቀደም ካለው ጊዜ እንስቶ እስከ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ድረስ በጎንደር ሳሉት አድባራት አለቃ የሚሾመው ከደብረ ብርሃን ሥላሴ በመሆኑ ግብር ይጫንለት ነበር:: አለቃው ሄደው አሰባስበው ያስገባሉ:: ዛሬ ደብሩ የሚተዳደረው በሰበካ ጉባኤ ነው:: የአካባቢው ነዋሪዎች በዓመት 12 ብር መክፈል ባለመቻላቸው ወደ 6 ብር ዝቅ እንዲል ተደርጓል:: በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኑን ከሚጎበኙ ሰዎች የሚገኝ ጥቂት ገንዘብና የባሕር ዛፍ እየለሙ በመሸጥ ቤተ ክርስቲያኑን ይደጉማሉ::

ስለ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ያገኘነው ታሪክ ይህንን ይመስላል:: የቤተ ክርስቲያኑ ታሪክ ሲነሣ ስሙ ስለሚወሳው ስለ አጼ ኢያሱ የተነገረውን ጠቅሰን ታሪኩን ብናጠቃልልስ:: አንድ ጊዜ አጼ ኢያሱ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሄዶ ሳለ ክፍለ ዮሐንስ የተባለ ሊቅ ሲጸልይ አግኝቶ ከኪሱ ያገኘውን ወርቅ አውጥቶ ወረወረና ሊቁን ሳያስበው መታው:: በዚህ ጊዜ ክፍለ ዮሐንስ የሚከተለውን ጉባኤ ቃና ወዲያው ሰጠ::

በእስጢፋኖስ አእባን እመንልቁ
ዘበማን ኢያሱ በወርቁ
/ድንጋዮች በእስጢፋኖስ ላይ ቢያልቁ
ኢያሱ መታኝ በወርቁ/

ምንጭ:— የቃል አስረጅ መምህር
ጌራወርቅ እንዳለው
-የአማርኛ [illegible] ቃላት
ሥርግው ሐብለ ሥላሴ /ዶ/ር/

www.ethiopianorthodox.org